


# የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቴክሳስ ተቋቋመ

ጁን 21 ቀን 2009 ዓ/ም

ኢትዮጵያን ከወያኔ ፋሽሽታዊ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በሚደረገው ፍልሚያ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር (ኢሕአግ) በአሁኑ ወቅት ጉልህ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል።

ለዚህ ትግል መሳካት በአለም ዙሪያ ያሉ ኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ወሳኝነት እንዳለው በመገንዘብ ኢሕአግ በተለያዩ ከተማዎችና ከፍለሀገሮች የድርጅቱን ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ላይ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው።

እኛም በቴክሳስ ክፍለሃገር የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ኢሕአግን አስመልክቶ ተከታታይ ስበሰባዎችን በማድረግ የጋራ መግባባት ላይ በመድረሳችን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቴክሳስ በዛሬው እለት ማቋቋማችንን ስንገልጽ በታላቅ ደስታ ነው።

በተሰጠን የኢሕአግ መመሪያ መሰረት ለድርጅታችን በመርሕ ላይ የተመሰረተ ድጋፍ እንደምናደርግ ቃል እየገባን በዚህ አጋጣሚ የቴክሳስ ቻፕተር አባል መሆን ለመትፈልጉ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሚከተለው ኢ-ሜይል አደራሻችን ማለትም፤ eppfTexas@gmail.com ትገናኙን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።

**አንድነት ሐይል ነው!!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቴክሳስ**

Email: info@eppfonline.org:    Website: www.eppfonline.org